Summer RISE
Connecting Students to Careers

# "Summer RISE 2021" የወላጅ/የሞግዚት ስምምነት

Partnerships Unit
MONTGOMERY COUNTY PUBLIC SCHOOLS
45 West Gude Drive, Room 2301, Rockville, Maryland 20850

## የወላጅ/ሞግዚት/ብቁ ተማሪ ስምምነት

የሠመር ራይዝ ፕሮግራም የተነደፈው በአሁኑ ወቅት በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት በመከታተል ላይ ለሚገኙ 11ኛ ክፍል ለሚገቡ እና ለ12ኛ ክፍል ተማሪዎች በሠመር ወቅት የሥራ ሙያ ልምዶችን ለመቃኘት የሚያስችል ነው።

1. በመገንዘብ ተስማምተዋል:- እርስዎ ወላጅ/ሞግዚት እንደመሆንዎ መጠን፥ በ 2021-2022 የትምህርት ዓመት በ MCPS 11ኛ ወይም 12ኛ ክፍል የሚገባ-የምትገባ ተማሪ ስለሚሳተፍበት-ስለምትሳተፍበት ሁኔታ የተስማሙ መሆንዎን ማረጋገጥዎን
2. በመገንዘብ ተስማምተዋል:- ተማሪው(ዋ) በተመደበ(ች)በት ቢዝነስ፥ ድርጅት፥ ኤጀንሲ ወይም ተቋም (the "Career Experience Host") site or virtually ("Career Experience") በሣምንት 10 ሠዓት፥ በቀን ከ 8 ሠዓት ያልበለጠ፥ በሣምንት ከ30 ሠዓት ያልበለጠ፥ እና ጠቅላላ በ 4 ሣምንት ቢበዛ 60 ሠዓት እየሠራ(ች) የሥራ ልምድ በመቅሰም እንደሚያሳልፍ/እንደምታሳልፍ። የ "Career Experience" በሣምንት አምስት ቀኖችን፣ ለአራት ሣምንት፣ ከጁላይ 5/2021 ጀምሮ እስከ ጁላይ 30/2021 መጨረሻ ይሠራል። Summer RISE ተሣታፊዎች ከሰኞ እስከ ዓርብ ከ 8:00 AM በፊት አይጀምሩም ወይም ከ6:00 PM በፊት ያጠናቅቃሉ። ከሙያ ልምምድ ሰጪው የሚመለከተው ባልደረባ/ቦች ("Career Experience Host Designee(s)") የሠመር ራይዝ ፕሮግራም " Summer RISE Program" ሲጠናቀቅ የ 40-ሠዓት የሙያ ልምምድ ማረጋገጫ ይሰጣሉ።
3. ተረድቼ ተስማምቻለሁ:- በ "Summer RISE Program" ለመሣተፍ፥ ተማሪዎች ቨርቹወል የሙያ ክህሎት ልምምድ እና የፋይናንስ ሊተረሲ አውደጥናት መሣተፍ እንዳለባቸው
4. ገብቶኝ ተስማምቻለሁ:- የ "Summer RISE Program" በአካል የሚሳተፉ ተሳታፊዎች ከያሉበት ቦታ የሙያ ተሞክሮ ልምምድ ወደሚያገኙበት ሥፍራ ለመመላለስ የመጓጓዣ አቅርቦት የራሴው ሃላፊነት መሆኑን። "Youth Cruiser SmarTrip® Cards" በሁሉም የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ ይገኛል።
5. በመገንዘብ ተስማምቻለሁ:- ለ "Summer RISE Program" ተሳታፊዎች ስለ ኮቪድ-19 የመከላከል እርምጃ፣ አካላዊ ርቀት መጠበቅ እና የፊት መሸፈኛ ጭምብል አጠቃቀምን ጨምሮ ስልጠና እንደሚወስዱ በአካል ለመሣተፍ የፊት መሸፈኛ ጭምብል መጠቀም አስፈላጊ መሆኑን። እንደአስፈላጊነቱ ለተማሪዎች ይሰጣል።
6. በመገንዘብ ተስማምተዋል:- በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) የ Summer RISE ፕሮግራም ሠራተኞች ለተመዘገቡት ተማሪዎች በሙሉ የሙያ ትምህርት ልምምድ/Career Experience ለመስጠት የተቻላቸውን ጥረት ሁሉ ያደርጋሉ፥ የሆነ ሆኖ፣ Career Experiences የቦታ መገኘትን መሠረት በማድረግ የሚወሰን ይሆናል። የ "Summer RISE Program" ሠራተኞች ተሳታፊ ተማሪዎችን በጅኦግራፊያዊ አመቺነት፣ በአካል እና/ወይም ቨርቹወል እንደአመቺነቱ እና ኢንዱስትሪ እንደተገኘ ለማቀናጀት ይሞክራል።
7. በመገንዘብ ተስማምተዋል:- የሠመር ራይዝ ፕሮግራም-Summer RISE Program ስንክልና ያላቸው ግለሰቦች የትምህርት ደምብ (Individuals with Disabilities Education Act (IDEA) እና በተጓዳኝ የሜሪላንድ ህግ መስፈርት መሠረት በሚፈለጉት ፕሮግራሞችና አገልግሎቶች ዉስጥ አልተካተተም።
8. በመገንዘብ ስምምነት ተደርጓል:- የሠመር ራይዝ ፕሮግራም " Summer RISE Program" ተሳታፊዎች የራሳቸውን መርኃግብር በቀጥታ ከ Career Experience Host Designee(s) ጋር የማስተባበር ሃላፊነት እንዳለባቸው የሙያ ልምምድ ሠዓቶች ከሰኞ እስከ ዓርብ 8:00 AM እና 6:00 PM መካከል ብቻ እንደሚሠራ።
9. በመገንዘብ ተስማምቻለሁ:- የ "Summer RISE Program" ተሳታፊዎች ጥሩ ክትትል የማድረግ ልምድ፣ ስነምግባር፣ ትክክለኛነት፣ ስነስርአት መጠበቅ፣ ሳይዘገይ ወዲያውኑ ማድረግ፣ ብስለት፣ ተገቢነት ያለው አለባበስ፣ አግባብ የሆነ የቢዝነስ ስነ-ምግባር ማሳየት እንደሚጠበቅባቸው እና ቨርችወል የሚሳተፍ/የምትሳተፍ ከሆነ፣ እንደሚታወቀው በቪድኦ እንደሚሆን በሠመር ራይዝ ፕሮግራም "Summer RISE Program" ተሳታፊዎች በ "Career Experience Host Designee(s)" አማካይነት የማይፈታ ጉዳይ ካጋጠማቸው ለ "Summer RISE program office" በኢሜይል summer-rise@mcpsmd.org ወይም በስልክ ቁጥር 240-740-5599 በመደወል ማሳወቅ አለባቸው።
10. ግንዛቤ እና ስምምነት ተደርጓል:- የሙያ ልምድ የሚሰጡ ክፍሎች ተጨማሪ የማጣርያ መስፈርቶች ለኖራቸው እንደሚችልና ጁላይ 5 የሠመር ራይዝ ፕሮግራም "Summer RISE Program" ከሚጀመርበት ቀን በፊት ተጨማሪ የምልመላ መስፈርት ማሟያ አስፈላጊ ከሆነ፥ የሠመር ራይዝ ፕሮግራም "Summer RISE Program" ተሳታፊዎች በቀጥታ ከሙያ ልምድ ሰጪ ተወካይ ጋር የመሥራት ኃላፊነት እንዳለባቸው
11. በመረዳት ተስማምቻለሁ:- የ "Summer RISE Program" ተሳታፊዎች አበላቸውን ለማግኘት ስለ ሠመር ራይዝ ፕሮግራም ተሞክሮአቸው የአጋማሽ-ጊዜ እና የፕሮግራም ማጠናቀቂያ የዳሰሳ ጥናት እንደሚሞሉ
12. በመገንዘብ ስምምነት ተደርጓል:- የሙያ ዝንባሌ እና ችሎታ የመሣሰሉት ከዝንባሌ ጋር በሚቀናጅበት ወቅት የተማሪው(ዋ) መረጃ ለሙያ ልምምድ ሰጪ ተወካይ አካል ይሰጣል። የሙያ ልምምድ ሰጪ ተወካይ ስለ ሠመር ራይዝ ፕሮግራም "Summer RISE Program" ተሳታፊዎች መረጃ የሚያገኙት እንደዝንባሌአቸው ለማዛመድ ሒደት እና/ወይም ከማን ጋር እንደተቀናጁ ለማወቅ ስለሚረዳ ነው። ከሠመር ራይዝ ፕሮግራም "Summer RISE Program" ተሳታፊዎች የሚሰበሰበውን መረጃ በሙሉ በሙያ ልምምድ ሰጪ ተወካይ "Career Experience Host and the Career Experience Host Designee(s)" አማካይነት ለሦስተኛ ወገን ተላልፎ አይሰጥም።

13. **ግንዛቤ በመውሰድ ስምምነት ተደርጓል፦** የሠመር ራይዝ ፕሮግራም "Summer RISE Program" ተሳታፊዎች ፕሮግራሙ ከተጠናቀቀ በኋላ የፕሮግራም ወጪ ማካካሻ በኤሌክትሪክ ቀጥታ ዲፖዚት $300 አበል የሚያገኙ ሲሆን የሠመር ራይዝ ፕሮግራም "Summer RISE Program" ሲጠናቀቅ MCPS ፈንዱን ለሚያስተዳድረው ባንክ የተማሪው(ዋ)ን የመጀመሪያ እና የመጨረሻ ስም ያስተላልፋል። የሠመር ራይዝ ፕሮግራም "Summer RISE Program" ተሳታፊዎች ቀደም ሲል ከባንኩ ተቋም ጋር አካውንት የሌላቸው ከሆነ፥ ባጀቱን በሚያስተዳድረው ባንክ ወይም ሌላ እነርሱ በሚመርጡት ባንክ አካውንት የመክፈት እድል ይኖራቸዋል። የሚሳተፉት ተማሪዎች አበላቸውን ማግኘት እንዲችሉ ቀጥታ ዲፖዚት የሚደረግበትን ቅጽ ሞልተው እንዲያቀርቡ እና በሙያዊ የክህሎት እና የፋይናንስ ሊተረሲ አውደጥናት/ዎርክሾፕ ላይ መሳተፍ አለባቸው። የባንክ አካውንት ለመክፈት የተለየ ችግር ካጋጠመ የሠመር ራይዝ ፕሮግራም "Summer RISE Program" ተሳታፊዎች ወይም የእነርሱ ወላጆች/ሞግዚቶች በእነርሱ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ወይም በ Summer RISE Program ጽ/ቤት የኮሌጅ እና ሙያዊ መረጃ/ኢንፎርሜሽን አስተባባሪን summer-rise@mcpsmd.orgወይም የስልክ ቁጥር፦ 240-740-5599 በመደወል መጠየቅ ይኖርባቸዋል።

14. **በመገንዘብ ተስማምተዋል፦** Summer RISE Program ተሳታፊዎች የሠመር ራይዝ ፕሮግራም "Summer RISE Program" በሚጠናቀቅበት ጊዜ በሙያዊ ልምድ ሰጪዎች ዘንድ ሥራ ለመቀጠር የይገባኛል ሁኔታ ስለማይኖር እንደሠራተኛ ለመቀጠር መጠበቅ/ተስፋ ማድረግ አይኖርባቸውም።

15. **በግንዛቤ ስምምነት ተደርጓል፦** የሠመር ራይዝ ፕሮግራም/Summer RISE Program ተሣታፊዎች የሰመር ራይዝ ፕሮግራም ሙያዊ ትምህርት ልምድ በሚወስዱበት ጊዜ የአሰሪዎቻቸው/Career Experience Hosts ተቀጣሪዎች ሊሆኑ አይችሉም። የሙያዊ ልምድ ሰጪዎች ከ Summer RISE Program ተሳታፊዎች የሥራ እንቅስቃሴዎች ወዲያውኑ ምንም አይነት የራሳቸውን ጥቅም/advantage አይወስዱም፣አንዳንድ ጊዜ ሥራቸውም ሊደናቀፍ ይችላል። የ Summer RISE Program ተሳታፊዎች በ Career Experience Hosts ሥራ ላይ በቀጥታ እንደማይሳተፉ ወይም በመደበኛነት እንደማይሠሩ፣ ወይም የዘወትር ሥራ (ለምሳሌ፦ ፋይል ማድረግ፣ ሌላ የጽህፈት ሥራቸውን መሥራት፣ ወይም ደንበኞቻቸውን ማስተናገድ) ላይ ጣልቃ እንደማይገቡ ግንዛቤ በማግኘት ተስማምተዋል። የሙያ ሥራ ልምድ ሰጪዎች ለተማሪዎች ስለ ቢዝነስ/ድርጅት እና በሥራ ድርሻ/ሚናዎች ላይ ያተኮረ፣ ኃላፊነቶች፣ እና ስለ ቢዝነሱ/የድርጅቱን የሥራ እንቅስቃሴዎች በሚመለከት ለተማሪዎች ሁሉአቀፍ ግንዛቤ ይሰጧቸዋል። ተማሪው(ዋ)/ተማሪዎቹ እነዚህን ሥራዎች በመሥራት ጥራት፣ ሙያ፣ እና ሥራ አስኪያጅን ወይም ማናጀር ውጤታማ ሆኖ የሚሠራበትን እና በበርካታ የሥራ ቅጥር አካባቢዎች ላይ ለመጠቀም የሚያስችል ጠለቅ ያለ መረዳት/እውቀት ይሻሉ።

16. **በመረዳት ተስማምተዋል፦** የሠመር ራይዝ ፕሮግራም "Summer RISE Program" ተሳታፊ በዚህ ስምምነት የተጠቀሱትን ስምምነቶች፣ በ Career Experience Hosts የተዘጋጁት ደንቦች እና መመሪያዎች፣ ወይም ሌላ ማናቸውም የሠመር ራይዝ ፕሮግራም "Summer RISE Program" ህጎች በ MCPS ድንጋጌ መሠረት ለመጠበቅ ካልቻለ(ች)፣ የሠመር ራይዝ ፕሮግራም ተሳታፊ ከፕሮግራሙ መባረር ይችላል/ትችላለች እና $300 አበልም ለማግኘት ብቁ አይሆንም/አትሆንም።

17. **በመገንዘብ ስምምነት ተደርጓል፦** እርስዎ ወላጅ/ሞግዚት እንደመሆንዎ መጠን፥ ለተማሪ የሠመር ራይዝ የሥራ ልምድ ሰጪው ተቋም "Career Experience Host" የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ድርጅት አይደለም። እንደነዚህ ዓይነት ድርጅቶች የሙያ ሥራ ልምምድ እንዲሰጡ (Career Experience Hosts) የሚመረጡት እነርሱ ለተማሪዎች የሚሰጡት የሙያ ልምድ የሚሻልና ተመራጭ ዕድል በመሆኑ፥ እና የሙያ ልምድ ሰጪዎቹ (Career Experience Hosts) ህጉን፥ የትምህርት ቦርድን ፖሊሲዎች፥ እና የ MCPS ደምቦችን የሚያከብሩ መሆናቸውን መሠረት በማድረግ ነው። ነገር ግን፥ MCPS እና/ወይም የሠመር ራይዝ ፕሮግራም ሠራተኛ የሙያ ሥራ ልምድ ሰጪውን እና ወይም የሥራ ሙያ ልምድ ሰጪው የወከለውን ተቋም አይቆጣጠሩትም።

18. **በመገንዘብ ተስማምተዋል፦** እርስዎ ወላጅ/ሞግዚት እንደመሆንዎ መጠን ተማሪው(ዋ) በሠመር ራይዝ ፕሮግራም ከመሣተፉ(ፏ) ጋር በተገናኘ ምክንያት ምንም አይነት ብልሽት ቢያጋጥም MCPS ተጠያቂ እንደማይሆን ተስማምቻለሁ።

## ተጨማሪ ስምምነት

**ተማሪ ኦንላይን ሲመዘገብ-ስትመዘገብ፣ ወላጅ/ሞግዚት የሚከተሉትን የተስማሙ መሆናቸውን ተማሪው ያረጋግጣል-ታረጋግጣለች**

- ❑ ተማሪው(ዋ) የሠመር ራይዝ ፕሮግራም "Summer RISE Program" በሚሣተፍበት-በምትሣተፍበት ወቅት ቪድኦ ለመቀረጽ፣ ፎተግራፍ ለመነሣት፣ እና/ወይም ሪኮርድ እንዲደረግ/እንድትደረግ ተፈቅዷል።እነዚህ ምስሎች እና/ወይም ሪኮርድ የተደረጉ ነገሮች ስለ ሠመር ራይዝ/Summer RISE ማስተዋወቅን ጨምሮ ምስሎቹን ለመጠቀም ማሳወቅ አስፈላጊ ሳይሆን ለተለያየ ዓላማ ጥቅም ላይ ሊውሉ ይችላሉ። በዚህ መልክ ጠቀሜታ ላይ ስለማዋላቸው ተማሪው(ዋ) ምንም ካሣ አይከፈለውም/አይከፈላትም እና MCPS ሁሉንም ምስሎች፣ ቪድዮዎች፣ እና የተቀረጹ/የተቀዱ ቁሳቁሶችን እና ከእነርሱ የተገኙ የሥራ ውጤቶችን የመጠቀም መብት አለው።
- ❑ የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ የሠመር ራይዝ ፕሮግራም (MCPS Summer RISE program) ባልደረባ ወይም የሙያ ሥራ ልምድ ሰጪ ተቋምን የወከለው Career Experience Host Designee(s) ተማሪው(ዋ) በሠመር ራይዝ (Summer RISE) ምዝገባ ወቅት የሰጠ(ች)ውን የግል (non-MCPS) ኢሜይል አድራሻ በመጠቀም ለተማሪው(ዋ) ኢሜል ያደርጋሉ።
- ❑ የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ የሠመር ራይዝ ፕሮግራም (MCPS Summer RISE program) ባልደረባ ወይም የሙያ ሥራ ልምድ ሰጪ ተቋምን የወከለው Career Experience Host Designee(s) በሠመር ራይዝ ምዝገባ ወቅት ከተማሪው(ዋ) የተሠጣቸውን የሥልክ ቁጥር በመጠቀም ለተማሪው(ዋ) ይደውላሉ ወይም ቴክስት ያደርጋሉ።

## ፊርማ

በሠመር ራይዝ ፕሮግራም/Summer RISE Program ለመሣተፍ የወላጅ/የሞግዚት ስምምነት መኖሩን ለማረጋገጥ የ "Summer RISE" ተማሪ የኤሌክትሮኒክ ፊርማ ይፈርማል/ትፈርማለች። በምዝገባ ወቅት፣ ጁላይ 2021 በድንገተኛ/አስቸኳይ ጊዜ ለማግኘት የሚቻል የወላጅ/የሞግዚት ስም፣ የስልክ ቁጥር፣ እና የኢ-ሜይል አድራሻ ያስፈልጋል።